"وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَى وَالْمَمَاتِ، وَمِنْ شَرِّ فِتْنَةِ الْمَسِيحِ الدَّجَالِ"

"ጌታዬ ሆይ! ከቀብር ቅጣት፣ ከጀሀነም ቅጣት፣ በሕይወት ላይና ከሞት ቡኃላ ከሚያጋጥሙ ፈተናዎች እንዲሁም ከመሲሂ-ደጃል ተንኮልና ፈተና በአንተ እጠበቃለሁኝ!"

ከማሰላመትህ በፊት አላህን የፈለግከውን በመጠየቅ ዱዐ ማድረግ ትችላለህ ለምሳሌ:-

"اَللَّهُمَّ أَعِنِّي عَلَى ذِكْرِكَ وَشُكْرِكَ وَحُسْنِ عِبَادَتِكَ"

"አላህ ሆይ! አንተን በማወደስ በማመስገን እና በጎ ባሪያህ በመሆን ላይ እገዘኝ!"

"اَللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْجَنَّةَ وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ النَّارِ"

"አላህ ሆይ! እኔ ጀነትን እጠይቅሃለሁ ከእሳትም በአንተ እጠበቃለሁ!"::

**(12)** ወደ ቀኝ ከዚያም ወደ ግራ በሁለቱም በኩል:-

"اَلسَّلَامُ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَةُ اللهِ"

"ሰላም በናንተ ላይ ይውረድ"

እያልክ አንገትህን በማዞር ሰላምታ አቅርብ::

**(13)** ሶላትህ ባለ ሶስት ረከአ እንደመግሪብ ወይም ባለአራት ረከአ እንደ ዙህር፣ አስር እና ኢሻእ ከሆነ ተሸሁድን አንብበህ ከጨረስክ ቡኃላ (በስእላዊ መግለጫ ቁ. 4 ላይ እንደሚታየው) ጉልበትህን በመመርኮዝ ከዚያም (በስእላዊ መግለጫ ቁ. 1 ላይ እንደሚታየው) እጆችህን ወደ ላይ በማንሳት ለሶስተኛው ረከአ "اَللَّهُ أَكْبَرُ" በማለት ቁም::

**(14)** የፋቲሀን ምዕራፍ ብቻ አንብብ በመቀጠልም ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው ሶላትህን ቀጥል:: ለመግሪብ ሶላት ሶስተኛው ረከአ መጨረሻ ላይ ለዙህር ለአስርና ለኢሻእ ሶላት አራተኛው ረከአ መጨረሻ ላይ ተሸሁድ አድርግ (ባለሁለት ረከአ ሶላት ላይ እንደነበረው) ትንሽ ለየት ባለ መልክ መጀመሪያው ተሸሁድ ላይ እንደተቀመጥከው ተቀመጥ:: እዚህ ላይ የግራ እግርህን ቀኝ እግርህ ስር በማድረግ የቀኝ እግርህን በማቆም



ወይም በማስተኛት መቀመጫህን መሬት ላይ ታሳርፋለህ (በሥእላዊ መግለጫው ቁ. 8 ላይ ካሉት ከሁለቱ አቀማመጦች አንዱን መምረጥ ትችላለህ) እዚያው ተቀምጠህ ባለህበት ከዚህ በፊት ሁለት ረከአ ሶላት ማጠቃለያ ላይ የሚባሉትን ብለህ በማሰላመት ሶላትህን ትጨርሳለህ::







__ከዚህ በፊት ያሳለፍናቸውን ሁሉ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቅ! በነርሱም ላይ ተረጋጋ!!__

**(15)** በእያንዳንድ ሙስሊም ወንድ ላይ አምስት ወቅት ሶላቶችን ስርአታቸውንና ደንባቸውን ጠብቆ በጀመአ መስጂድ መስገድ ግዴታ ይኖርበታል:: ስለዚህ በአላህ ፈቃድ ማንኛውም ሰው ከሙናፊቂኖች (ከእሳት ከዳኑት) ጋራ እንዲሆን እዚህ ላይ መሳነፍ ወይም መዘናጋት የለበትም::

**(16)** እያንዳንዱ ሙስሊም ወንድም ሆነ ሴት ጉዞ ላይ ባልሆኑበት ወቅት አስራ ሁለት ረከአ ተጨማሪ ሶላቶችን መስገድ ይወደድላቸዋል:: እነሱም:- ከፈጅር ሶላት በፊት ሁለት ረከአ፣ ከዙህር ሶላት በፊት አራት ረከአ፣ ከበስተኋላው ሁለት ረከአ፣ ከመግሪብ ሶላት ቡኃላ ሁለት ረከአ፣ ከኢሻእ ሶላት ቡኃላ ሁለት ረከአ ሲሆን __ረሱላችን ሶለሏሁ አለይሂ ወሰለም የነዚህን ሶላቶች ደረጃ በተመለከተ:-__ "በአንድ ቀንና ሌሊት ውስጥ አስራ ሁለት ረከአ የሰገደ በነሱ ምክንያት ለሱ በጀነት ቤት ይገነባለታል" ብለዋል:: (ሙስወሊም 728) በጉዞ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ግን የዙህር፣ የመግሪብ እና የኢሻእን ሱናዎች በመተው የፈጅርን ሱናና ዊትርን ይሰግዳል::



**(17)** የአንዳንድ ሰጋጆች የተወሰኑ ስህተቶች:-

1-በጋራ በሚሰገድበት ጊዜ ተከታዩ ኢማሙን መሽቀዳደም ወይም ከሱ ጋራ እኩል መንቀሳቀስ

2-ሶላት በመስገድ ላይ እያሉ በዓይን ወደ ሰማይ ማንጋጠጥ




## የጀናዛ ሰላት አሰጋገድ

**(1)** በሟች ላይ ለመስገድ እቅድ በማድረግ የሶላት መክፈቻ ተክቢራን (በስእላዊ መግለጫ ቁ. 1 ላይ እንደሚታየው) እጅህን በማንሳት "اَللَّهُ أَكْبَرُ" በል::



ሁለት እጆችህን (ከቁ. 2 ስእላዊ መግለጫዎቹ ውስጥ እንደ አንዱ በማድረግ) ደረትህ ላይ ካደረክ ቡኃላ የፋቲሀን ምእራፍ አንብብ::

**(2)** እንደመጀመሪያው እጆችህን ወደ ላይ በማንሳት ለሁለተኛ ጊዜ "اَللَّــهُ أَكْبَــرُ" በማለት



ተክቢራ አድርግ

እንደመጀመሪያው እጆችህን ደረትህ ላይ አድርግ ከዚያም ሶላት አለነቢይን (ሶ.ዐ.ወ.) አንብብ

**(3)** እጆችህን ወደ ላይ በማንሳት ለሶስተኛ ጊዜ "اَللَّهُ أَكْبَرُ" በማለት ተክቢራ አድርግ

እጆችህን ወደ ደረትህ መልስ ከዚያም ለሟቹ በሚከተለው ዱዓ ምህረት ጠይቅለት:-

"اَللَّهُمَّ اغْفِرْ لِحَيِّنَا وَمَيِّتِنَا وَشَاهِدِنَا وَغَائِبِنَا وَصَغِيرِنَا وَكَبِيرِنَــا وَذَكَرِنَا وَأُنْثَانَا، اللَّهُمَّ مَنْ أَحْيَيْتَهُ مِنَّا فَأَحْيِهِ عَلَى الْإِسْلَامِ وَمَنْ تَوَفَّيْتَهُ مِنَّا فَتَوَفَّهُ عَلَى الْإِيمَانِ"

"አለህ ሆይ! በሂወት ላለነውም ለሞቱትም በቅርብ ለምንገኘውም ለራቁትም ለትንሹም ለትልቁም ለወንዱም ለሴቱም ምህረት አድርግልን! አላህ ሆይ! ከኛ በሂዎት የምታቆየውን በኢስላም አቆየው ከኛም የምትገለውን በኢማን ላይ ግደለው!"

**(4)** እጆችህን ወደ ላይ በማንሳት ለአራተኛ ጊዜ "اَللَّهُ أَكْبَرُ" በማለት ተክቢራ አድርግ

እጆችህን ከዚህ በፊት እንደነበሩት ወደ ደረትህ መልስ ከዚያም:-

"اَلسَّلَامُ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَةُ اللهِ" በማለት አሰላምት

__የአሏህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) ጀናዛን አስመልክተው እንዲህ አሉ:-__ "ጀናዛ ላይ ሶላት በመስገድ የተገኘ ሰው (ቂራጥ) አለው እስኪቀበር ድረስ የተገኘ ደግሞ ሁለት (ቂራጥ) አለው" ሲሉ ሁለት (ቂራጥ) ምንድን ነው? በማለት ጠየቋቸው እሳቸውም:- "ሁለት ትልልቅ ተራሮችን የሚያክል (ምንዳ) ነው አሏቸው" (ቡኻሪ1325 ላይ ሙስሊም ደሞ 945 ላይ ዘግበውታል) "ጀናዛን (በመቅበር) ላይ ፈጣን ሁኑ (ከመቅበር አታዘግዩ ምክንያቱም ሟቹ) ጥሩ (ሰው) ከነበረ ማፋጠኑ (ለርሱ) ጥሩ ነው:: ከዚህ ውጪ ከነበረ ደግሞ ከራሳችሁ ላይ የምታርቁት መጥፎን ነው" (ማለታቸውን ቡኻሪ 1315 ሙስሊም ደሞ 944 ዘግበውታል)

رقم سجل لدى الادارة العامة للبحوث، والتأليف، والترجمة بالأزهر الشريف (17898)



بسم الله الرحمن الرحيم



የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል:

﴿إِنَّ الصَّلَاةَ كَانَتْ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ كِتَابًا مَوْقُوتًا﴾ النساء- 103

"ሰላት በምእመናን ላይ በግዚያት የተወሰነች ግዴታ ናት"

የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል:

- "የሰላትን ደንብና ስነስርዐት በመጠባበቅ የሚሰግድ የትንሳኤ ቀን ብርሀን መረጃና ከእሳት የመዳን ምክንያት ትሆንለታለች" ኢማም አህመድ 6540 ዳረሚ 2721 ዘግበውታል
- "በሰውየውና በክህደት እንዲሁም በሽርክ መካከል ያለው ልዩነት ሰላትን መተው ነው" ኢማም አህመድ 82 ዘግበውታል
- "እኔ ስሰግድ እንዳያችሁት አድርጋችሁ ስገዱ" ኢማም ቡኻሪ 631 ዘግበውታል

# አጠር ባለ መልኩ የተዘጋጀ የነብዩ ሰለሏሁ አለይሂ ወሰለም የሰላት አሰጋገድ ስነስርአት




# صفة صلاة النبي ﷺ

-باختصار-

باللغة الأمهرية
-إثيوبيا-

بلغات العالم *50 لغة*
غازي بن علي سلطان الداغستاني
المتخرج من الجامعة الإسلامية بالمدينة المنورة
المدينة المنورة +966504352709
1432/2011 +201115587559

(1) ለአላህ መስገድ ካሰብክ ሙሉ ጦሃራ ላይ በመሆን በሶላትህ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የትም ቦታ ብትሆን በሙሉ ሰውነትህ ወደ ቂብላ -ካእባ- መዞርና ለመስገድ ያሰብከውንም ሶላት ፈርድም ሆነ ሱና በልቦናህ ለይተህ ኒያን ማስገኘት ይኖርብሃል::




(2) ተክቢረተል ኢህራም ማለትም የሶላት መክፈቻ ተክቢራን በል (ይህን ስትል አይንህን ሱጁድ በምታደርግበት ቦታ ላይ በማሳረፍ በሁለት መዳፎችህን ሁለት ትከሾችህ ወይም በሁለት ጆሮችህ አቅጣጫ በስእላዊ መግለጫው ቁ. 1 ላይ እንዳለው) አድርገህ "اَللَّهُ أَكْبَـرُ"

"አሏህ ከሁሉም በላይ ታላቅ ነው" በማለት ይሆናል::

(3) ከዚያም ቡኃላ በምትቆምበት ጊዜ ሁለት እጆችህን ደረትህ ላይ አድርግ (ይህንን ስታደርግ የቀኝ እጅህ የግራ እጅህ ላይ ይሆናል ከቁ. 2 ስእላዊ መግለጫዎቹ ውስጥ እንደ አንዱ በማድረግ) የሚከተለውን የመክፈቻ ዱዓ አንብ:-




"سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ، وَتَبَارَكَ اسْمُكَ، وَتَعَالَى جَدُّكَ، وَلاَ إِلَهَ غَيْرُكَ"

"ጌታዬ ሆይ ከጉድለት ሁሉ የጠራህ ምስጋና የተገባህ ስምህን በማውሳት በረከት የሚገኝ ልቅናህ ከፍ ያለ ከአንተ በስተቀር አምላክ የለም"

ከዚያም እንዲህ በል:-

"أَعُوذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ"

"ከተረገመው ሸይጣን በአሏህ እጠበቃለሁ!"

በመቀጠል ሱረቱል ፋቲሃን አንብብ:-

﴿بِسْمِ اللهِ الرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ(١) اَلْحَمْدُ لِلَّه رَبِّ الْعَـالَمِينَ(٢) اَلرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ(٣) مَالِك يَوْمِ الدِّينِ(٤) إِيَّاكَ نَعْبُـدُ وَإِيَّـاكَ



نَسْتَعِينُ(٥) اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ(٦) صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلاَ الضَّآلِّينَ(٧)﴾ "آمِينْ"

﴿በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩሕሩሕ በጣም አዛኝ በኾነው በመታገዝ እጀምራለሁ ምስጋና ለአሏህ ይገባው የዓለማቱ ጌታ ለኾነው እጅግ በጣም ሩሕሩሕ በጣም አዛኝ የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው አንተን ብቻ እንገዛለን አንተንም ብቻ ርዳታ እንለምናለን ቀጥተኛውን መንገድ ምራን የነዚያን በርሱ ላይ በጉ የዋልክላቸውን በነርሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ﴾ "ምራን!!"

ቀጥሎም በቃል የምታውቀውን የቁርአን አንቀፅ አንብብ::

(4) ሩኩዕ አድርግ (ይሄንን ስታደርግ ሁለት መዳፎችህን ወደ ሁለት ትከሾችህ ወይንም ሁለት ጆሮችህ አቅጣጫ ካነሳህ ቡኃላ ስእላዊ መግለጫው ቁ. 1 ላይ እንደሚታየው:- "اَللَّـــهُ أَكْبَـــرُ" በማለት አጎብድድ::)




በሩኩእህ ላይ ጭንቅላትህ በጀርባህ ትይዩ መሆን አለበት የእጆችህን ጣቶች በመዘርዘር (በስእላዊ መግለጫው ቁ. 3 ላይ እንደሚታየው) እጆችህን ጉልበትህ ላይ ማኖር ግድ ይሆንብሃል::

ከዚያም ሶስት ጊዜ:-

"سُبْحَانَ رَبِّيَ الْعَظِيمِ"

"ታላቅ የሆነው ጌታዬ ከጉድለት ሁሉ የጠራ ነው" በል::

(5) (ሁለት እጆችህን በስእላዊ መግለጫው ቁ. 1 ላይ እንደሚያሳየው ወደ ላይ በማንሳት) እራስህን ከሩኩእ "سَمِعَ اللَّهُ لِمَنْ حَمِدَهُ" "አሏህ የአመስጋኞችን ምስጋና ሰሚና ተቀባይ ነው" በማለት ከፍ አድርግ::

ከቆምክም ቡኃላ:-

"رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ، حَمْدًا كَثِيرًا طَيِّبًا مُبَارَكًا فِيه"

"ጌታችን ሆይ ብዛት ያለው ጥሩና የተባረከ የሆነ ምስጋና ላንተ ይሁን" በል::

(6) ሱጁድ "اَللَّـــهُ أَكْبَـــرُ" እያልክ ውረድ:: ከቻልክ



ጉልበቶችህን ከእጆችህ አስቀድም (በስእላዊ መግለጫው ቁ. 4.1-4.4 ላይ እንደሚታየው) የእግሮችህንና የእጆችህን ጣቶች ወደ ቂብላ በማዞር የእጆችህን ጣቶች ገጥመህ በትከሾችህ ወይም በጆሮችህ አቅጣጫ በማኖር ጡንቻዎችህን ከጎንህ ሆድህን ከጭኖችህ ማራቅ ይኖርብሃል::




በሁለት ጉልበቶችህ መካከልም ክፍተት መተው አለብህ:: (ሴትም እንደዚህ ነው የምታደርገው ነገርግን ሰውነቷን መሰብሰብ ይኖርባታል) ሱጁድህ በሚከተሉት የሰውነት አካል ላይ መሆን አለበት:- ግንባር ከአፍንጫ ጋር፣ ሁለት መዳፎች፣ ሁለት ጉልበቶች እና የሁለት እግር ጣቶች ውስጣዊ ክፍል (በስእላዊ መግለጫው ቁ. 5.1-5.4 ላይ እንደሚታየው)




በዚሁ ሱጁድ ላይ እንዳለህ ሶስት ጊዜ:

"سُبْحَانَ رَبِّيَ الْأَعْلَى"

"የበላይ የሆንከው ጌታ ጥራት ይገባህ" በል::

በሁሉም ሱጁዶችህ አላህን የምትፈልገውን በመጠየቅ ዱዐ ማድረግ ትችላለህ (አረበኛ ቋንቋን የማታውቅ ከሆንክ በቋንቋህ ዱዓ ልታደርግ



ትችላለህ::)

(7) እራስህን ከሱጁድ "اَللَّـــهُ أَكْبَـــرُ" በማለት ቀና አድርግ:: ክዚያም ተቀመጥ (የግራ እግርህን በማንጠፍ ተቀመጥበትና የቀኝ እግርህን አቁመው ወይንም በኮቴህ ላይ መቀመጥ ትችላለህ ሁለት እጆችህን ጉልበቶችህ ወይም ጭኖችህ ላይ አስቀምጥ በስእላዊ መግለጫው ቁ.6 እንደሚታየው)




ቀጥለህም ሁለት ጊዜ:-

"رَبِّ اغْفِرْ لِي"

"ጌታዬ ሆይ ማረኝ" በል::

(8) ለሁለተኛ ጌዜ "اَللَّهُ أَكْبَـرُ" በማለት ሱጁድ ውረድ (በስእላዊ መግለጫው ቁ. 5.1-5.4 እንደሚታየው) በመቀጠልም ሶስት ጊዜ:-

"سُبْحَانَ رَبِّيَ الْأَعْلَى" በል::

(9) እራስህን ከሱጁድ አንሳና ከቻልክ (በስእላዊ መግለጫው ቁ. 4 እንደሚታየው) በጉልበቶችህ በመመርኮዝ ለሁለተኛው ረከአ:- "اَللَّهُ أَكْبَرُ" እያልክ ቁም::

(10) ሱረቱል ፋቲሀንና ሌላ ከቁርአን የቀለለህን አንብብ (እጆችህን ቀ. 2 ስእላዊ መግለጫ ላይ ካለው እንደ አንዱ አደራረግ አድርግ) ከዚያም በመጀመሪያው ረከአ ላይ ያደረከውን ሁሉ ፈጽም::

(11) የምትሰግደው ሶላት ባለ ሁለት ረከአ እንደ ሶላተል ፈጅር የጁምአ ሶላት እና ሁለቱ የኢድ ሶላቶች አይነት ከሆነ ከሁለተኛው ሱጁድ ከተነሳህ ቡኃላ ተቀመጥ (በስእላዊ መግለጫው ቁ. 7 እንደሚታየው)









ከዚያም ተሸሁድን አንብ:-

"اَلتَّحِيَّاتُ لِلَّه، وَالصَّلَوَاتُ وَالطَّيِّبَاتُ، اَلسَّلاَمُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللهِ وَبَرَكَاتُهُ، اَلسَّلاَمُ عَلَيْنَا وَعَلَى عِبَادِ اللهِ الصَّالِحِينَ. أَشْهَدُ أَن لاَّ إِلَهَ إِلاَّ اللهُ، وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ"

"የመከባበሪያ ሰላምታዎች፣ ስግደቶችና መልካም ስራዎች ሁሉ ለአላህ (ብቻ የተገቡ) ናቸው:: አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ የአላህ እዝነትና በረከት እንዲሁም ሰላም በእርሰወ ላይ ይስፈን:: ሰላም በኛም ላይ እና ደጋግ በሆኑት ባሮቹ ሁሉ ላይ ይሁን:: ከአላህ በስተቀር እውነተኛና ትክክለኛ አምላክ አለመኖሩን በማመን የምስክርነት ቃሌን እሰጣለሁኝ እንዲሁም ሙሀመድ የአላህ ቅን አገልጋይና መልክተኛ መሆናቸውንም እመሰክራለሁኝ!"

ቀጥለህም የሚከተለውን በል:-

"اَللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ، اَللَّهُمَّ بَـــارِكْ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا بَارَكْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ"

"አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትና ምህረትን እንዳወረድከው በሙሀመድና በሙሀመድ ቤተሰቦች ላይም እዝነትና ምህረትን አውርድ አንተ ምስጉንና የላቅክ ጌታ ነህና:: ጌታዬ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ በረከትን እንዳወረድከው በሙሀመድና በሙሀመድ ቤተሰቦች ላይም በረከትን አውርድ አንተ ምስጉንና የላቅክ ጌታ ነህና"

በመቀጠልም እንዲህ በማለት ከአራት ነገሮች በአላህ ተጠበቅ:-

"اَللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، وَمِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ،